የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | |
|---|---|
| 13 ኛ ዓመት ቁጥር 13 | ሐረር ታህሳስ 22 ቀን 2001 ዓ/ም |
| 13 th Year No. 13 | HARAR Dec.31, 2008 |

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ ብር 2.10<br>Unit Price Birr 2.10 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፓ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 83/2001 ዓ/ም

የሐረሪ ፊደል አፃፃፍ ስርዓትን በአዲስ መልክ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ ገጽ 638


## አዋጅ ቁጥር 83/ 2001 ዓ.ም
## የሐረሪ ፊደል አፃፃፍ ስርአትን በአዲስ መልክ ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ባሐረሪ ፊደልና አፃፃፍ ስርአት ላይ እንዲሁም በቋንቋው ዙሪያ ያጋጠሙትን ችግሮች በሳይንሣዊ ዘዴ በመፍታትና በተገኙ ተጨባጭ መልካም ተሞክሮዎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ፤

በሐረሪ ፊደልና አፃፃፍ ስርአት ላይ የህብረተሰቡን አመለካከት ባህልና ስነ-ልቦና እንዲሁም የፊደላት ኢኮኖሚያዊነት፣ ቴክኖሎጂና ስነ-ትምህርታዊ መመዘኛዎችን በማገናዘብ፤

በተሻሻለው የሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ-መንግሥት አንቀጽ 59 (1) መሠረት በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ይህን አዋጅ አውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹ የሐረሪ ፊደልና አፃፃፍ ስርአትን በአዲስ መልክ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 83/2001 ዓ.ም ››ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. ‹‹ ሐረሪ ሀርፊ ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 የተገለፀው የሐረሪ ፊደል ገበታ ነው።
2. ‹‹ጉባኤ›› ማለት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49(1)(ለ) መሠረት የተቋቋመው የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ነው ፡
3. ‹‹ንጥረ ድምጽ /Phoneme ››ማለት አንድ ቃል ከሌላው የሚለይበት የንግግር ድምጽ ነው።
4. ‹‹ፊደል/Character/››ማለት የሐረሪ ቋንቋን ለመፃፍና ለማንበብ የምንጠቀምበት ምልክት ነው።
5. ‹‹አካዳሚ›› ማለት በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት የተቋቋመ የሐረሪ ቋንቋ ጥናትና ምርምር አካዳሚ ነው።

## 9. ቃላት በሳድስ አለመጀመራቸው

የሐረሪ ቃላት ሲፃፉ በሳልስ (በሦስተኛው ሖሔ) እንጂ በሳድስ (ስድስተኛው ሖሔ) አይጀመርም፡፡

## 10. በራብዕ የሚጨርሱ ቃላት አፃፃፍ

1. በሐረሪ ማንኛውም የቅርብና የቅርብ ሩቅ ጊዜ ግስ በተባእት ፆታ በአውንታ ሲነገር የቃሉ መጨረሻ ፊደል ‹‹ግዕዝ›› (በአንደኛው ሖሔ) ይሆናል፤ የሚለው መመሪያ ቀርቷል፡፡
2. የግስ ቃላት ወይም የሌሎች ቃላት መጨረሻ ራብዕ ሆኖ ወይም ሐምስ ሆኖ ወይም ሌላ ሆኖ ቃሉ ጥያቄ መሆኑን ወይም መገረም ወይም ለስላቅ መሆኑን ወይም ለሌላ መሆኑን ለማመልከት ካስፈለገ አግባብ ባለው ስርዓተ- ነጥብ መለየት ይቻላል፡፡
3. በራብዕ ድምጽ የሚነበቡ ፊደላት መፃፍ ያለባቸው በራብዕ ፊደል ብቻ ነው፡፡

## 11. ስርአተ-ነጥብ

1. ሐረሪ የሚጠቀምበት ስርአተ ነጥብ በአካዳሚ ተጠንቶ በይፋ የሚገለጽ ይሆናል፡፡
2. ከላይ በአንቀጽ 11 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወሰነው ስርዓተ-ነጥብ በተቻለ መጠን ከሌሎች የሳባ ፊደል ተጠቃሚ ቋንቋዎች የተቀራረበ ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 12. የሐረሪ ቁጥር ፊደላት

የሐረሪ ቁጥር ፊደላት ለአፃፃፍ በሚያመቸውና የአረብኛ ቁጥር የሚባለውን የቁጥር ፊደል ማለት (1.2.3 .) ይጠቀማል፡፡

## 13. የሙያዊ ቃላት አሰያየም

በየጊዜው የሚሰየሙ አዳዲስ ሙያዊ ቃላት አካዳሚው ከሚያሳትማቸው መዝገበ-ቃላት ውጭ ከሆኑ፡-

ሀ. በጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት በአካዳሚ መጽደቅ አለባቸው፡፡

ለ. በግልጋሎት ላይ ያሉ ሙያዊ ቃላት ላይ ማስተካከያ ሲደረግም ማስተካከያው ይፋ ከመሆኑ በፊት ለአካዳሚው ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

## 14. የተሻሩ ሕጎች

1. የሐረሪ ቋንቋ ፊደላትና የቋንቋውን አፃፃፍ ስርአትን ወጥ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 18/1991 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ እና የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ፡፡

## 15. የአካዳሚው ኃላፊነት

አካዳሚው አዋጁን ማስተዋወቅ፤ማስተማርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በመስራት የማስፈጸም ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 16. ልዩ ኃላፊነት

የክልሉ ከፍተኛ አመራር አካላት ፣የፖለቲካ ተሿሚዎች፣ የህዝብ ተመራጮችና የመንግስት ሰራተኞች በተለይ ቋንቋውን የሚናገሩት ከዚህ የማሻሻያ አዋጅ ጋር ራሳቸውን ቀድሞ ማስተዋወቅና ለአዋጁ ተግባራዊነት ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆን አለባቸው ፡፡

## 17. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ደንብ የቋንቋ አካዳሚው አዘጋጅቶ ለጉባኤው ጽ/ቤት የማቅረብ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 18. የመተባበር ግዴታ

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 19. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በጉባኤው ከፀደቀበት ከታህሳስ 22 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

ሐረር -ታህሳስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት